የሐዋርያት ሥራ መግቢያ

1. ከ12ቱ ሐዋርያት ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው?
ሀ) ስምዖን ቀነናዊ ለ) ልብድዮስ ሐ) ማርቆስ መ) በርተሎሜዎስ

2. የጌታ የምሥጢር ሐዋርያት የሚባሉት እነማን ናቸው?
ሀ) ጴጥሮስ እና ጳውሎስ
ለ) ዮሐንስ፣ ያዕቆብ እና ጴጥሮስ
ሐ) ዮሐንስ እና ጴጥሮስ
መ) ማቴዎስ፣ ሉቃስ፣ ማርቆስ እና ዮሐንስ

3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን እየዞሩ እንዲያስተምሩ ሲያዛቸው ከመከራቸው ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ) መከራን እና ሞትን እንዳይፈሩ
ለ) እንደ እባብ ጠቢባን እንዲሆኑ
ሐ) እንደ ርግብ የዋሃን እንዲሆኑ
መ) መልሱ አልተሰጠም

4. ከሐዋርያት መካከል በመጀመሪያ የተጠራው የቱ ነው?
ሀ) ጳውሎስ ለ) ዮሐንስ ሐ) እንድርያስ መ) ጴጥሮስ

5. ከሐዋርያት መካከል የስማዕትነትን አክሊል መጀመሪያ የተቀዳጀው የቱ ነው?
ሀ) እስጢፋኖስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) ዮሐንስ መ) ያዕቆብ

6. በአስቆሮቱ ይሁዳ ምትክ የሐዋርያትን ማህበር የተቀላቀለው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ማትያስ ለ)ማቴዎስ ሐ)ማስያስ መ)በርናባስ

7. ከሚከተሉት ውስጥ ስለ ሐዋርያው እንድርያስ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጌታችንን ለማየት የፈለጉ አሕዛብ ግሪካውያንን ወደ ጌታ በማቅረቡ የአሕዛብ ወዳጅ ሐዋርያ ተብሏል
ለ) የጌታን ማደርያ ካየ በኋላ ለወንድሙ ለጴጥሮስ በመንገሩ የቤተሰብ ሐዋርያ ተብሏል
ሐ) ከሰው ጋር የመግባባት ችሎታ ስለነበረው በሐዋርያት ዘንድ እንደ አስተባባሪ ይቆጠር ነበር
መ) ሁሉም መልስ ናቸው

8. የጌታ ደቀመዛሙርት “ክርስቲያን” የሚለውን ስም ያገኙት በየት ከተማ ነው?
ሀ) አንጾኪያ ለ) እስክንድርያ ሐ) ኢየሩሳሌም መ) ገሊላ

9. ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ የሞቱን ነገር ሲነግራቸው “አይሁንብህ” በማለት የተከራከረው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ዮሐንስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) ያዕቆብ መ) ይሁዳ

10. ከሚከተሉት ውስጥ የወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ ስም ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ቦኣኔርጌስ ለ) አቡቀለምሲስ ሐ) ታኦሎግስ መ) ፍቁረ እግዚእ ሠ) ፕሮቶክሌቶስ

11. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታን ከመከተላቸው በፊት በዓሳ አሥጋሪነት ከሚታወቁ ሐዋርያት ውስጥ የማይመደበው የቱ ነው?
ሀ) ጴጥሮስ ለ) ያዕቆብ ሐ) ሌዊ መ) ዮሐንስ

12. ከሐዋርያት መካከል ሞትን ያልቀመሰው የቱ ነው?
ሀ)ጴጥሮስ ለ)ይሁዳ ሐ)ዮሐንስ መ)ሁሉም ሞትን አይተዋል

13. ናትናኤልን ወደ ጌታ ያቀረበው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ፊልጶስ ለ) ዮሐንስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ወደ ጌታ የመጣው በራሱ ነው

14. ከሚከተሉት ሐዋርያት ውስጥ መልእክታትን ያልጻፈው የቱ ነው?
ሀ) ዮሐንስ ለ) ታዴዎስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ያዕቆብ ሠ) ሁሉም መልእክታትን ጽፈዋል

15. “ጌታ ሆይ አብን አሳየንና ይበቃናል።” ብሎ የጠየቀው ሐዋርያ የቱ ነው?
ሀ) ዮሐንስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) ፊልጶስ መ) ይሁዳ

16. ከሰዱቃውያን ወገን የሆነው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ)ማቴዎስ ለ)ዮሐንስ ሐ)ናትናኤል መ)ቶማስ

17. ከሚከተሉት ውስጥ ስለማቴዎስ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?
ሀ) የቀድሞ ስሙ ሌዊ ሲሆን የጌታ ሐዋርያ ከመሆኑ በፊት ቀራጭ ነበር
ለ) በአስቆሮይቱ ይሁዳ ምትክ የተተካ ሐዋርያ ነው
ሐ) ሐዋርያ ሳይሆን ጌታን እየተከተሉ ይማሩ ከነበሩ አርድዕቶች መካከል አንዱ ነበር
መ) ጌታችን ካረገ በኋላ የተነሳ ሐዋርያ ነው

18. ከሚከተሉት ውስጥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከጠራቸው ሐዋርያት ውስጥ አይመደብም?
ሀ) ማትያስ ለ) ታዴዎስ ሐ) በርተሎሜዎስ መ) ስምዖን ሠ) መልስ የለም

19. ከሐዋርያት ውስጥ የቁም ተዝካሩን አውጥቶ ጌታን የተከተለው የትኛው ነው?
ሀ) ማቴዎስ ለ) ጴጥሮስ ሐ) ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ መ) ያዕቆብ ወልደ ዘብዴዎስ

20. የሐዋርያት 12 መሆን ምሳሌነቱ የማይሆነው ምንድነው?
ሀ) የ12ቱ ነገደ እስራኤል
ለ) ኤልያስ መሰዊያ አድርጎ በሰራቸው 12 ድንጋዮች
ሐ) ኢያሱ የዮርዳኖስን ወንዝ ለመሻገር የተጠቀማቸውን ድንጋዮች በወሰዱት ሰዎች
መ) 12ቱ ካህናተ ሰማይ

21. ሐዋርያትን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በላካቸው ጊዜ እንዲይዙ ያዘዛቸው የቱን ነው?
ሀ) በትር ለ) ወርቅ ሐ)ሀ እና ለ መ) አንድ እጀጠባብ

22. ግመል በመርፌ ቀዳዳ ያሳለፈው ሐዋርያ ማን ነው?
ሀ) ቶማስ ለ) ታዴዎስ ሐ) ጴጥሮስ መ) ያዕቆብ

23. ከሚከተሉት ሐዋርያት መካከል ከሌላ መጠሪያ ስሙ ጋር በትክክል ያልተዛመደው የቱ ነው?
ሀ) ስምዖን ቀነናዊ- ናትናኤል
ለ) ይሁዳ- ታዴዎስ(ልብድዮስ)
ሐ) ቶማስ- ዲዲሞስ
መ) ያዕቆብ- አቡቀለምሲስ

24. ከሐዋርያት መካከል ወንድማማቾች የሆኑት የትኞቹ ናቸው?
ሀ) ጴጥሮስ እና እንድርያስ
ለ) ያዕቆብ እና ዮሐንስ
ሐ) ያዕቆብ እና ይሁዳ
መ) ሀ እና ለ
ሠ) ለ እና ሐ

25. ከሚከተሉት ሐዋርያት መካከል ጌታችን ስም ያወጣው ለየቱ ነው?
ሀ) ስምዖን- ጴጥሮስ ለ) ስምዖን- ናትናኤል ሐ) ቶማስ- ዲዲሞስ መ) ሀ እና ለ ሠ) ሁሉም መልስ ናቸው

26. ከሚከተሉት ውስጥ የሐዋርያት ስልጣን የሆነው የቱ ነው?
ሀ) የማሰር እና የመፍታት
ለ) በዳግም ምጽዓት ጊዜ በዙፋን ላይ ተቀምጦ በ12ቱ ነገደ እሥራኤል ላይ መፍረድ
ሐ) የማስታረቅ(የማማለድ)
መ) ሁሉም መልስ ናቸው